## 1. በጦላይና በባሪ የተፈጠረው ግጭት ጋብ ማለቱ ታወቀ

በጦላይና በባሪ ለአንድ ሳምንት ያክል የዐማሮችን ቤትና ንብረት በጅምላ መቃጠሉና የሰው ሕይወት ሲጠፋ መሰንበቱ ተዘግቧል:: ድርጊቱ የተፈፀመው ከነሐሴ 5 እስከ 11 /2009 ዓ.ም ነው:: ከአስር በላይ ሰዎችም በገጀራና በጥይት ተደብድበው መገደላቸውን የአይን እማኞች ከስፍራው ገልጸዋል። ከመንግስት አካላት ውጭ ህብረተሰቡ በድርጊቱ አለመሳተፉንም ምንጮቹ አስረድተዋል።በአካባቢው የነበሩት የክልሉ ፖሊሶች ችግሩን ከመፍታት ይልቅ ሰዎችን በጥይት መተው ገድለዋል። የጦላይ ጦር ማሰልጠኛ ተቋምም በአካባቢው ያለ ቢሆንም ግጭቱን ለማስቆም አለመሞከራቸው ታውቋል።የአካባቢው ባለስልጣናት አብሮ የኖረን ህዝብ ከማጋጨት እንዲቆጠቡም የጦላይ ነዋሪ የሆኑ የአማራ ተወላጆች ጠይቀዋል። በ አሁኑ ሰ ኣት ግጭቱ ጋብ ማለቱ ታውቋል:: ጉዳቱን ያደረሱት ከሚሊሻዎች፣ ከግብርና ሠራተኞች፣ ማዳበሪያ ከሚያከፋፍሉ ሰዎችና ከወረዳ ኃላፊዎች ሠላሳ የሚሆኑ የተደራጁ አካላት መሆናቸውን ጋዜጠኛ ሙሉቀን ተስፋው ኦገስት 18-2017 ዘግቧል:: ችግሩ የተፈጠረው ኣንድ የኣማራ ተወላጅ በመሬት ይገባኛል ጥያቄ ሲሚገት ቆይቶ ከተፈረደለት በኋላ መሆኑ እንዲሁ ተዘግቧል:: ወያኔና አጋሮቹ ከዚህ በፊትም በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች አማራውን ሲገድሉና ሲያፈናቅሉ መኖረቸው የሚታወቅ ነው። ህዋሃት ሆን ብሎ የእልቂት ኣዋጅ ያወጀበት ኣማራው በሚኖርበት ኣካባቢ ሁሉ ችግር ሲደርስበት በፍጥነት መረጃ የሚያደርስ ኣውታር ማቋቋም ኣስፈላጊ መሆኑን በርካታ ኣስተያየት ሰጪዎች ተጠቁመዋል:: የየብሔር ሽማግሌዎችና ፀረ ህዋሃት ታጋዎች ብሔር ብሔርሰቦች ከዘረኝነት ጥላቻና ግጭት እንዲታቀቡ ምክርና መመሪያ እንዲሰጡ ተጠይቀዋል::

**********

2. የጎሳ ፌዴሬሽን መቶ በመቶ ዘረኝነት ነው: ሰማንያ ጎሳ ባለባት ኢትዮጵያ ፍጹም የጎሳ ፌዴራሊዝም ሊፈጠር አይችልም ሲሉ ፕ/ር ጌታቸው ኃይሌ ገለፁ

እንደ ፕሮፌሰር ጌታቸው አገላለፅ የጎሳ ፌዴሬሽን መመሥረት ዘረኝነትን በይፋ ማንገሥ ነው። አንዳችን ከሌላችን የተለየን መሆናችንን በሐሰት መመስከራችን ነው። በኢትዮጵያ የተዘረጋው የጎሳ ፌዴራሊዝም ሳይሆን የወያኔዎችንና የኦሮሞ ፖለቲከኞችን ፍላጎት ማርኪያ ነው። ሰማንያ ጎሳ ባለባት አገር ላይ ፍጹም የጎሳ ፌዴራሊዝም ሊፈጠር አይቻልም። በየክልሉ ውስጥ ብዙ ጎሳዎች አሉ። ግን ክልሉ የነሱ አገር አይደለም፤ አገር የላቸውም፥ የኦሮሞዎች፥ የአማሮች፥ የትግሬዎች ጥገኞች ናቸው። በክልሉ ላይ መንግሥት ከተቋቋመ መንግሥቱ የኢትዮጵያውያን ሁሉ መሆኑ ቀርቶ የኦሮሞች፥ የአማሮች፥ የትግሬዎች መንግሥት ነው የሚሆነው። የኦሮሞ፥ የአማራ፥ የትግራይ መንግሥት አቋቁሞ የሌሎቹን መብት መጠበቅ አይቻልም። አንድ አካባቢ የኦሮሞ፥ የትግራይ፥ የአማራ አገር ነው ሲባል፥ በብዛት የሰፈሩበትን ሰዎች ለማመልከት ነው እንጂ፥ የሰፈሩበት መሬት የነሱ ነው ማለት አይደለም። መሬቱ ማንም ኢትዮጵያዊ ሊኖርበት መብት ያለው የኢትዮጵያ መሬት ነው። በስማቸው የተጠራውን መሬት "የኛ መሬት ነው" ብለው ሌላውን ከዚያ ሊያስወጡት፥ የእኩልነት መብቱን ሊነፍጉት፥ ወይም ከመሬቱ ቈርጠው ለሌላ አገር ሊሸጡለት፥ ወይም ይዘውት ሊሄዱ አይችሉም ሲሉ ሐሳባቸውን ቋጭተዋል ፕ/ር ጌታቸው ኃይሌ:: ማብራሪያውን የሰጡት የኦሮምያ ክልልና የኣዲስ ኣበባ ግኑኙነት ላይ ያላቸውን በሰጡበት ኦገስት 18-2017 ባቀረቡት ኣጭር ጽሑፍ ነው::

*********

## 3. የአውሮፓ ህብረት የኬንያ የምርጫ ውጤት በኦንላይን እንዲለቀቅ ጠየቀ

የአውሮፓ ህብረት የታዛቢዎች ቡድን በኬንያ ነሐሴ 8/2017 የተደረገውን ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ በወረቀት የሰፈሩ ቅጾችና የድምጽ ውጤቶች በድህረ-ገጽ በመልቀቅ ፤የምርጫውን ግልጽነትና ትክክለኛነት ማሳየት እንዲቻል ለኬንያ ምርጫ ኮሚሽን ጥሪ አቀረበ፡፡ የአውሮፓ ህብረት ኮሚሽን ቃል አቀባይ የሆኑት አንድሪው ሊሞ እንዳሉት ከ 41 000 የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ 2 900 የሚሆኑት በድህረ-ገጽ ይፋ ተደርገዋል።የኬንያ ምርጫ ኮሚሽን ሁሉንም የመራጮች ድምጽ የያዘ ሰነድ ይፋ እንዲያደርግ ጠይቀዋል፡፡ ምርጫውን ከታዘቡት አለም አቀፍ ተቋማት መካከል የአውሮፓ ህብረት አንዱ ነው ። በወቅቱ የሰጠው መግለጫም "ምርጫው ነፃና ፍትሀዊ" ነው የሚል ነበር። በምርጫው ፕሬዚዳንት ሁሩ ኬንያታ በ 54.3 ፐርሰንት ዳግም ማሸነፋቸውን የምርጫ ኮሚሽኑ ይፋ ቢያደርግም 44.7 ፐርሰንት ድምጽ አግኝተዋል የተባሉት ተቀናቃኙ ራይላ ኦዲንጋ ውጤቱን አልቀበልም ብለዋል።ጉዳዩን ወደ ፍ/ቤት ወስደው እንደሚሞግቱም አስታውቀዋል። በድህረ ምርጫው በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች ተቀስቅሶ በነበረው ግጭት በርካታ ሰዎች ሞተዋል።ኬንያ አሁን ወደ ቀድሞ ሰላሟ መመለስ ችላለች።

*******

## 4. በስፔን -ባርሴሎና ሐሙስ ምሽት በደረሰው የሽብር ጥቃት በርካታ ሰዎች ሞቱ

*አንድ ስፔናዊ ወጣት የወንድሙን ዶክመት ተጠቅሞ የጭነት መኪና በመከራየት በባርሴሎና ወስጥ እግሮኞች በሚበዙበት ጎዳና በማሽከርከር 14 ሰዎችን ሲገድል ከ100 በላይ የሚሆኑት ጉዳት ደርሶባቸዋል። ነሐሴ 17/2017 ጥቃቱ የተፈጸመው ቱሪስቶች በሚበዙበት አካባቢ በመሆኑ ከ30 በላይ ሀገራት ዜጎች የጥቃቱ ሰለባ ሆነዋል።ለጥቃቱም ራሱን "እስላማዊ መንግሥት" ብሎ የሚጠራው አሸባሪ ቡድን ሀላፊነት ወስዷል። ስፔን የ3 ቀናት ብሔራዊ ሐዘን አውጃለች።የተለያዩ ሀገራት መሪዎችም የሀዘን መግለጫ መልዕክት በማስተላለፍ ላይ ናቸው። ፖሊስ ከጥቃቱ ጋር ግንኙነት ሳይኖራቸው አይቀርም ያላቸውን አራት ግለሰቦች በቁጥጥር ሥር አውሏል።*

*በሌላ በኩል በካምብሪልስ ከተማ በሁለት ሰዓታት ልዩነት ተመሳሳይ ጥቃት መድረሱንም የስፔን ፖሊስ ገልጿል።በጥቃቱ 7 ሰዎች ሲቆስሉ የአንድ ሰው ህይወት አልፏል።በተሽከርካሪ ጥቃት ያደረሱት አምስት ተጠርጣሪዎችን ተኩሶ መግደሉን ፖሊስ አስታውቋል።*

*ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአውሮፓ ከተሞች አሸባሪዎች ተሽከርካሪን በመጠቀም ጥቃት እያደረሱ መሆኑ ይታወቃል።*

---

## 5. የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዘረኝነትን አወገዘ

*የተባበሩት መንግስታት ዋና ጸሀፊ አንቶኒዮ ጉቴሬዝ ነሐሴ 16/2017 በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ዘረኝነትን፣ ዚኖፎቢያና ፀረ-ሴማዊነትን አወገዙ።ሰሞኑን በቨርጂኒያ አሜሪካ "የነጭ የበላይነትን" በሚያቀነቅኑ ቡድኖች የተፈጠረውን ግጭትም በጽኑ አውግዘዋል።ዘረኝነት በሁሉም አካባቢ እያቆጠቆጠ ነው።በጋራ ሆነን ልንዋጋው ይገባል።የመቻቻልና የመከባበር እሴቶቻችን ለማጥፋት የሚጥሩ ቡድኖችን ከወዲሁ መከላከል ይኖርብናል ። ሁሉም ሰው ዘረኝነትን በመጸየፍ መቻቻልን፣መከባበርንና ልዩነቶችን በመቀበል የተሻለች አለም እንድትኖረን መስራት ይኖርበታል በማለት ጥሪ አስተላልፈዋል።*

## 6. ቡናን አዘውትሮ መጠጣት ለጤና ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ጥናቶች ጠቆሙ

*ለብዙ ሀገራት የኢኮኖሚ ዋልታ የሆነው ቡና፤ በቀን አንድ ሲኒ መጠጣት ከፍተኛ የሆነ የጤና ጠቀሜታ እንዳለው ጥናቶች አመልክተዋል። ቡና በውስጡ በያዘው "ካፌይን" የተባለው ንጥረ-ነገር አዕምሯችንን በማነቃቃት ስራዎቻችን በትኩረትና በቅልጥፍና ለማከናወን እንደሚረዳን ተገልጿል።በዩናይትድ ኪንግደም አልሚስ ፋውንዴሽን ከፍተኛ ሳይንቲስት የሆኑት ዶክተር ሉሲ ቻምበርስ በጥናታቸው እንዳረጋገጡት፤ ቡና ወይም ሻይ አዘውትሮ መጠጣት እድሜን ይጨምራል:በስኳር በሽታ የመያዝ አደጋን ይቀንሳል::በጉበት በሽታ በቀላሉ ከመጋለጥ ይከላከላል እንዲሁም ከልክ ያለፈ ውፍረትን እንደሚቀንስ ጥናቱ አሳይቷል።እንደ ጥናቱ ከሆነ ሁለትና ከዚያ በላይ ብርጭቆ ሻይ መጠጣትም ከአንድ ሲኒ ቡና የሚገኘውን ካፌይን እንደሚተካ አሳውቋል።ሬድ ቡል የተባለው አነቃቂ መጠጥ ከቡና ጋር እኩል የካፌይን ይዘት ቢኖረውም፤ በውስጡ 10 ግራም ስኳር እንዳለው ተጠቁሟል።*

7. በ7 ኪ. ወርቅ የተሰራው ኮምፒውተር በአንድ ሚሊዮን ዶላር ለገበያ ቀረበ

ፕራይም ኮምፒውተር የተባለ ኩባንያ ተቀማጭነቱ በስዊዘርላንድ ነው። ከደምበኞቹ የሚቀርቡለትን የተቀናጡ ምርቶች ጥያቄ ለመመለስ በማቀድ ያመረተውን በ18 ካራት ወርቅ የተሰራ አዲስ አይነት ዴስክቶፕ ኮምፒውተር ባሳለፍነው ሳምንት በአንድ ሚሊዮን ዶላር፣ በተባበሩት አረብ ኤሜሬትስ ለገበያ አቀረበ።

በዱባይ ከዚህ ቀደምም ከወርቅ የተሰሩ የአፕልና የብላክቤሪ ምርቶች ለገበያ ቀርበውም ነበር። *በዱባይ ጁሜራህ የሚገኘው እና* በአገሪቱ እጅግ ዝነኛ እንደሆነ በሚነገርለት "ቡርጂ አል አረብ ሆቴል" ደምበኞቹ በቆይታቸው የሚጠቀሙበትን ባለ 24 ካራት ወርቅ አይፓድ በነጻ እንደሚሰጥም *ዘገባው* አመልክቷል፡፡